# ዓርማ የሌለውን ሰንደቅ ዓላማ መጠቀም የሚከለክል ረቂቅ ሕግ ተዘጋጀ

Wednesday, 24 June 2009   http://www.ethiopianreporter.com/content/view/5693/54/

በጋዜጣው ሪፖርተር



"ሰንደቅ ዓላማው አንድ ዓይነት ብቻ ስለመሆኑ" የሚደነግግ አርማ የሌለው ሰንደቅ ዓላማ ማዘጋጀትንና መጠቀምን የሚከለክልና የሚቀጣ ረቂቅ ሕግ ለፓርላማ ቀረበ፡፡ በመጀመሪያ ንባብ ደረጃው የእንግሊዝኛ ትርጉሙ ጭምር እንዲቀርብ ታዞ ወደ አመንጭው ተመለሰ፡፡

በአዋጅ ቁጥር 18/88 የተደነገገውን አርማ ያልያዘ ሰንደቅ ዓላማ እስከ አሁን ድረስ በተለያዩ ስፍራዎች ሥራ ላይ ሲውል መታየቱን ይህ አሰራር ደግሞ የሰንደቅ ዓላማውን ሕግ በትክክል ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑን እንደሚያገናዝብና አርማ የሌለው ሰንደቅ አለማ ብሔራዊ ነው አርማ ባይኖረውም መጠቀም ይቻላል የሚል አስተሳሰብ እንዲሰፍን ማድረጉን የረቂቅ አዋጁ ማብራሪያ ገልጾ አዲሱ ማሻሻያ ይህንን የተንሰራፋ እምነት ያስከተለውን የአዋጁን ጎደሎ ለማረም መዘጋጀቱን ያስረዳል፡፡

በረቂቅ ሕጉ መሰረት ሰንደቅ ዓላማው አንድ ዓይነትና አንድ አይነት ብቻ መሆኑን፣ ዓርማ የሌለው አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ አለመሆኑን አርማውን ሲያካትቱ መጠቀም የቀለማቱን ቅደም ትከተልና መጠን እንዲሁም ብሔራዊ አርማውን ሳይጠብቁ ማዘጋጀትና መገልገል የተከለከለና የሚያስቀጣ መሆኑን የሚወስነው ረቂቅ ሕጉ ሌሎች የተከለከሉ ተግባራትንም ይዘረዝራል፡፡ ስለዚህም ሰንደቅ ዓላማውን ብሔራዊ ሀዘን ሲታወጅ ከተመለከተው ከሕግ አግባብ ውጪ ባንዲራውን በሐዘን ወይም በቀብር ስነስርዓት መጠቀም እንዲሁም በስብሰባ ወይም በማንኛውም መሰል ክንውኖች ሰንደቅ ዓላማውን የጠረጴዛ ሽፋን አድርጎ መጠቀም የህንፃ መሸፈኛ ማድረግን ይከለክላል፡፡ ተፈጽሞ ሲገኝም በገንዘብ መቀጮና እስከ አንድ ዓመት ተኩል በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ የተለያዩ ጥናቶችና ምክክሮች ሲካሄድበት የቆየ ስለመሆኑ አሁን ያሉትን የሰንደቅ አላማ አጠቃቀም ጉልህ ችግሮች በመለየትና

በመገንዘብ፣ እንዲሁም ደግሞ ከፌዴራል አገራት መካከል የናይጀሪያ የካናዳና የህንድን የሰንደቅ አላማ ህግጋት ልምድና ተሞክሮ በመውሰድ የተዘጋጀ ስለመሆኑ በተነገረለት በዚህ ረቂቅ ከተካተቱ አዳዲስ ድንጋጌዎች መካከል አንዱ መስከረም በገባ በሁለተኛው ሳምንት ሰኞ የሰንደቅ አላማ ቀን እንዲከበር የሚወስነው ነው።

መስከረም የአዲስ ዓመት መባቻ ኅብረተሰቡ አዲስ እቅድ የሚይዝበት የሚነሳሳት በወሩ በዓላት የማይበዛበት በመሆኑ እንደተመረጠ የሚገልፀው ረቂቅ ሕግ የሰንደቅ አላማችን በሕዝብ በዓላትና እረፍት ቀናት የሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ስለመካተቱ ወይም "ታስቦ ብቻ" የሚውል ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም።

በደርግ ዘመን የወጣው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የሰንደቅ ዓላማ ህግ ሰንደቅ ዓላማው ከሌሎች አገራት ሰንደቅ ዓላማዎች ከሌሎች አርማዎች/ምልክቶች ጋር ሲወጣ የሚኖረውን አወጣጥ ስነስርዓት ይደነግግ የነበረ ሲሆን፣ የአሁኑ የሰንደቅ ዓላማ ህግ ይህን ያስተዋወቀው ገና አሁን ነው።

አንድ ርዕሰ ብሔርና ወይም መራሔ መንግሥት ሲሞት የሚኖረውን የሰንደቅ ዓላማ አሰቃቀል ስነ ስርዓትና ሐዘንን በተመለከተ ከንጉሠ ነገስቱ የመጀመሪያ መከራ በረቂቅ ሕግ ደረጃ የተደረገው ከዚህ የሰንደቅ ዓላማ ማሻሻያ ሕግ ከሳምንታት በፊት ቀደም ብሎ ለፓርላማው ቀርቦ በነበረው ከኃላፊነት የተነሱ የአገርና የመንግሥት መሪዎች መብቶችን ጥቅሞች ለመወሰን በተረቀቀው የሕግ ሃሳብ ውስጥ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ባለው በዚህ የሕግ ረቂቅ እንደተቀመጠው ከኃላፊነት የተነሳ ፕሬዚዳንት ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በመላው አገሪቱ የአንድ ቀን ብሔራዊ ሐዘን ይታወጃል። የአገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ በፌዴራልና በክልል መሥሪያ ቤቶች ህንጻዎች በትምህርት ቤቶች ወዘተ.እና ውጭ አገር ባሉ የአገሪቱ ኤምባሲዎች ዝቅ ብሎ ይውለበለባል። ፕሬዚዳንቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ምክትሉ በኃላፊነት ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ "በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጻሚ ይሆናሉ" የተባለው የቀድሞ መሪዎችን መብትና ጥቅም ለመወሰን በተዘጋጀ ሕግ ረቂቅ እግረ መንገዱን ነው።

በሌላ በኩል የሰንደቅ ዓላማው ረቂቅ ሕግ በኃላፊነት ላይ ያለ ወይም ከኃላፊነት የተነሳ የአገር ወይም የመንግሥት መሪ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ ሰንደቅ ዓላማው በሚታወጀው ብሔራዊ የሀዘን ቀን ዝቅ ብሎ እንደሚውለበለብ ይወስናል።

ከፕሬዚዳንቱ ከጠቅላይ ሚኒስትሩና ከምክትሉ ውጪ ብሔራዊ የሀዘን ቀንና ሰንደቅ አላማው ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባቸውን ሁኔታዎች የሚወስነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መሆኑን የሰንደቅ ዓላማ ሕግ ማሻሻያ ረቂቅ "በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የብሔራዊ የሀዘን ቀኑ በህዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላት በሚውለበለብበት ጊዜ ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ አይውለበለብም" ይላል።

በዋነኛነት ሰንደቅ ዓላማው "አንድ ዓይነት ብቻ ስለመሆኑ"ና መሆኑን ለመወሰን የቀረበው ረቂቅ ሲፀድቅ ባለፉት መንግሥታት ኢትዮጵያ ውስጥ

በተቋቋመው ልማድና አሰራር እንዲሁም በሕግ የነበሩትን ሌሎች የሰንደቅ ዓላማ ዓይነቶች ያስቀራል፡፡ ከዚህ በፊት በነበረው አሰራርና ሕግ መሰረት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አርማ የሌለው ባለ አርማና ባለመርገፍ የሚባሉ ዓይነቶች ነበሩት፡፡